# ከጓደኛቸው እጅ ያመለጠች የ150ሺ ብር እድል

ፀሀይ ለምድር የምትሰጠው ብርሃን ቀርቶ፣ ሰው ሰራሽ የውጭ መብራቶች ለአካባቢው ብርሃናቸውን እየለገሱ ናቸው፡፡ ነፋሻማው የጥቅምት ወር አየር እየነፈሰ ነው፡፡ አንዳንዱ ወደ ቤት ለመሄድ ቸኩሏል፡፡ አንዳንዱ ወደ ማታ ትምህርቱ ለመሄድ እየነጎደ ነው ከጊዜ ጋር ትግል ገጥሞ፡፡ ብቻ ሁሉም በየፊናው እየተጣደፈ ነው ፡፡



አቶ ስዩም ቸሬ
በዕድል ሎተሪ
150,000.00 ብር

በመስከረም ወር ውስጥ በአንዱ ቀን ማታ 1፡00 ሰዓት አካባቢ ከጓደኞቻቸው ጋር ቀጠሮ ይዘዋል፡፡ እግረ መንገዳቸውን ትንሽ ለመጨዋወት፣ በዚያውም በስራ ምክንያት ወደ መተማ የሚሄደውን ጓደኛቸው የወጪ ሊላቸው፡፡ ሙዚቃ በቤቱ ቢንቆረቆርም ቀልባቸው በነገው ጉዞ ላይ ነው፡፡

ከጓደኛቸው ጋር ቀጠሮ የያዙት ስድስት ኪሎ አካባቢ ካለ ከአንዲት ግሮሰሪ ነበር፡፡ እዚያም ተገናኝተው አንድ ሁለት ማለት ጀመሩ፡፡ ሳቅ ጨዋታው ደርቷል፡፡ እንደዚህ በሳቅ ጨዋታ መንፈሳቸው እየረካ እያለ ሎተሪ አዟሪ አጠገባቸው ይመጣል፡፡ ሎተሪ አዟሪው የተለያዩ የሎተሪ አይነቶችን በእጁ ይዟል፡፡ ዕድል ሎተሪን በመዳፉ እንደያዘ እጁን ዘረጋ፡፡ ሰውየው ቀደም ሲል የገዙትን ሎተሪ ለሎተሪ አዟሪው አሳዩት፡፡ ማስተዛዘኛ አለው፡፡ ሎተሪ አዟሪው ወደ ጓደኛቸው እጁን ዘረጋ፡፡ ዝም አለ፡፡ ጓደኛቸው እንዲቆርጥ ጠየቁት፡፡ "አይ እኔ ባለ አንድ ብሩ /መደበኛ/ይሻለኛል "በማለት ባለ አንድ ብሩን ነጠላ ቲኬት ይቆርጣሉ፡፡ እሳቸው ግን ጓደኛቸው አልቆርጥም ያለውን ዕድል ሎተሪ ቆረጡ፡፡ ይህ ከሆነ ቀናት አለፉ፡፡

እሁድ ዕለት ከዘመዶቻቸው ጋር በመሆን ለቅሶ ደርሰው ይመለሳሉ፡፡ ፀሀይ መቷቸዋል፡፡ ውሃ ጥም ይዟቸዋል፡፡ ጊዮርጊስ አካባቢ ሲደርሱ የቴሌ ጡረተኞች ክበብ ውሃ ጥማቸውን ለመቁረጥ አብረዋቸው ያሉ ሰዎች ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡ አይ ከዚያ ይልቅ ከፊት ለፊቱ ካለው ሆቴል እንግባ በማለት ያቀረቡት ሃሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ወደዚው

ሄዱ፡፡ ከዚያም እሺ እናንተ ግቡና ጠብቁኝ ብለው ጫማ ለማስጠረግ ወደ ኋላ ቀረት ይላሉ፡፡

ጫማ እያስጠረጉ እያለ ሎተሪ አዟሪ ባጠገባቸው ያልፋል፡፡ መጀመሪያ የመደበኛ ሎተሪ ማውጫን ያያሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዕድል ከሳቸው ጋር አይደለችም፡፡ ትዝ ሲላቸው ዕድል ሎተሪ ከጓደኛቸው ጋር ሆነው ቆርጠዋል ፡፡

"ከትላንት ወዲያ የወጣው ሎተሪ ማውጫ አለህ; "አሉት

" አዎ የዕድል ሎተሪ ነው ; አለኝ " በማለት ማውጫውን እንዲያዩት ሰጣቸው ፡፡

የያዙትን ሎተሪ ማውጫው ጋር ካሉት የዕድል ቁጥሮች ጋር አስተያዩ፡፡

ማውጫውን ለሎተሪ አዟሪው መለሱለት፡፡ ቲኬቷን ግን ወደ ኪሳቸው መለሷት፡፡ ጫማቸውን አስጠርገው ወደ ሚጠበቋቸው ጓደኞቻቸው ከመሄዳቸው በፊት አንደኛው ጓደኛቸው ይከታተላቸው ኖሮ ፊታቸው በሀሴት ሲፈካ አይቶ

"ምን ተፈጥሮ ነው ይላቸዋል"

እሳቸውም "አይ የሆነ ነገር ተገኝቶ ነው" ይሉትና ጉዳዩን ይነግሩታል፡፡ ከዚያም አንድ ሁለት እያሉ ወደ ሚጠብቋቸው ጓደኞቻቸው ተያይዘው ሄዱ፡፡ መዝናኛው ቤት እንደገቡ አብሯቸው ላለው ጓደኛቸው

"ግርማ እስቲ ይሄን ቁጥር ደውለህ ና" ብለውት የዕድል ቁጥሮችን ይነግሩታል፡፡እንደተነገረውም አጣርቶ ይመጣል፡፡ እንደመጣም "የሰጠሽኝ ቁጥር ተዘግቷል" ይላቸዋል፡፡ ጫር ይባባላሉ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን አጠገባቸው ያሉት ሰዎች ግራ ገብቷቸዋል፡፡

ባለቤታቸውም "እናንተ ሰዎች ምን አግኝታችሁ ነው;" ሲሉ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

"አይ ምንም አይደለም ዝም ብለን ነው" ይሏቸዋል፡፡ ውሃ ጥማቸውን እንዳረኩ ወደ ቤት በታክሲ መንዝ ይጀምራሉ፡፡ ታክሲ ውስጥ እንዳሉ ለባለቤታቸው "ዛሬ አንድ ጥሩ ዜና ይዣለሁ፡፡"

"ምንድነው;" ቢላቸው

"አይ ቤት ስንደርስ ነው የምንገርሽ" በማለት የልብ ምታቸውን ይጨምራሉ፡፡ ቤት ሲደርሱ ልጆች ቴሌቪዥን እየተመለከቱ እየተጫወቱ ያገኛቸዋል፡፡ ለቤተሰብ አባላት ልጆች ድህነት ደህና ሰንብት በሉ በማለት የምስራቹን ይነግሯቸዋል፡፡ ቤቱ በደስታ ይሞላል፡፡ በነጋታው ከቢሮቸው ሄደው ለጓደኛቸው ይነግሩታል፡፡ ያ አልቆርጥም ያለው ጓደኛቸው መተማ ሄዷል፡፡

“ተሼ እስቲ  ይሄን ማውጫና የሎተሪውን ቲኬቱን አሰተያያልኝ” በማለት ለጓደኛቸው ይሰጡታል፡፡ ጓደኛቸውም

“ እኔ አላምንም….. ! እኔ አላምንም…..!” በማለት ይጮሃሉ ፡፡

“እንዴት አታምንም በአይንህ እያየህ” ሲሉ ይመልሱሉታል ፡፡

ከላይ ያነበብነው ታሪክ የ150,000 ብር ዕድለኛ የሆኑት የአቶ ስዩም ቸሬ ነው፡፡ ጥቅምት 12፣ 2003 ከወጣው የዕድል ሎተሪ በሁለተኛ ዕጣ አሸናፊ ናቸው፡፡ ነዋሪነታቸው በአዲስ አባበ ስድስት ኪሎ ያሬድ ት/ቤት አካባቢ ሲሆን የቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ሰራተኛ ናቸው፡፡ ስለዕድላቸው ተጠይቀው በጣም ደስ እንዳለቸው ገልጸው ባገኙት ገንዘብ ቤት ለመስራት እንዳሰቡ ነግረውናል፡፡ እኛም ቤት ለእንቦሳ ለማለት ተመኝተናል፡፡